የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

# የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምላሽ አሰጣጥን (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው የ965 ላቦራቶሪ ምርመራ በዕለቱ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች አለመኖራቸው ተረጋግጧል።

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 10,736 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 965 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 0 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 90 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 0 |
| በአጠቃላይ ያገገሙ | 21 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 3 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 116 |

በዛሬው ዕለት ምርመራ ከተደረገላቸው 965 ሰዎች መካከል ምንም በኮሮና ቫይረስ የተያዘ ሰው አለመገኘቱ በሀገራችን ያለውን የኮቪድ 19 በሽታ የስርጭት መቀነሱን ሳይሆን ይልቁንም ናሙና የተወሰደላቸው ሰዎች በቫይረሱ እንዳልተያዙ የሚገልጽ መሆኑን በመገንዘብ ሕብረተሰቡ እስካሁን ሲያደርጋቸው የነበሩ የበሽታውን መከላከያ ዘዴዎችን በጥብቅ ማሳታዎስ እንወዳለን::

በተጨማሪም ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት:

- በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች በአፋጣኝ በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲያሳውቁ፣
- ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ቦታ መሰባሰብ በማስወገድ፣ እጅን አዘውትሮ በመታጠብ፣ በአካል ንክኪ የሚደረግ ሰላምታን በመተውና አካላዊ መራራቅን ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንዲከላከል እናሳስባለን።

በማንኛውም ሰዓት ጥቆማ ለመስጠትና መረጃ ለማግኘት በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር
ሚያዝያ 15 ፣ 2012 ዓ.ም